# ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

| | |
|---|---|
| የተዛመዱ ርእሶች፡- | ACA, ACF, ACH, ACH-RA, GKA-RA, JFA, JFA-RA, JHC, JHC-RA, JHF, JHF-RA |
| ሃላፊ ፅ/ቤት፡- | የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ<br>የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ<br>ዋና የሥራ ሃላፊ |

## *ፆታዊ ወከባ*

## I. ኣላማ

ስለ *ፆታዊ ወከባ* መመርያ የመተግበርያ ሂደቶች ለማቅረብ

## II. ፍቺ

A. *ፆታዊ ወከባ በ1964 የሲቪል መብቶች ኣዋጅ፣ Title VII፣* በ1972 እና በ1991 እንደተሻሻለ፣ እና *በ1972 የትምህርት ኣዋጅ፣ Title IX* መስረት በፆታ የተመሰረተ ህገወጥ የኣድልዎ ገፅታ ነው።

*ፆታዊ ወከባ* ፍቺው ያልተፈለገ የፆታ ኣቅርቦት፣ የፆታ ችሮታ ጥያቄዎች፣ እና ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ የቃል፣ የፅሁፍ፣ ወይም ፆታዊ ባህርይ ያለው ኣካላዊ ስነምግባር ከዚህ በታች ባሉት ሁኔታዎች የሚካሄድ ነው፡-

1. ለእንደዚህ ኣይነት ስነመግባር እሺ ሲባል፣ በግልፅ ወይም በሚስጢር፣ ለመቀጠር ወይም ለትምህርት፣ ወይም በሌሎች የት/ቤት እንቅስቃሴዎች ፈቃድ

2. ለዚህ ኣይነቱ ስነምግባር በኣንድ ግለሰብ እሺ ወይም እምቢ መባልን ኣጥቂው/ዋ ይህን የፆታ ኣቅርቦቶች የደረሰበ(ባ)ትን ግለሰብ የሚነኩ የስራ ወይም የኣካዴሚያዊ ውሳኔዎች ለማድረግ ከተጠቀመ(ች)በት

3. የዚህ ኣይነቱ ስነምግባር በግለሰቡ/ቧ ስራ እና/ወይም ኣካዴሚያዊ ኣፈፃፀም ላይ ተቀባይነት በሌለው ሁኔታ ጣልቃ ሲገባ ወይም ኣስፈሪ፣ ጥለኛ፣ ወይም ኣስከፊ የስራ ወይም የመማር ኣካባቢ ሲፈጥር

B. *ፆታዊ ሁከት* የሚመለከተው ኣካላዊ ፆታዊ ድርጊቶች ከግለሰብ ፈቃድ ውጭ ላይ ወይም ኣንድ ግለሰብ ፈቃደኛ ለመሆን በማይ(ት)ችልበት (ለምሳሌ፣ በግለሰቡ/ቧ እድሜ ወይም በእፆች ወይም በኣልኮል በመጠቀም ምክንያት፣ ወይም ፈቃድ የመስጠት ችሎታ የማያስችል የኣእምሮ ወይም በሌላ ስንክልና) ሁኔታን ነው።

## III. ቅደም-ተከተሎች

የተወሰኑ የፆታዊ ወከባ ፎርሞች በወንጀል ቅጣቶች ወይም በልጅ ማንሳቆል የሚያስከትሉ ወንጀለኛ ስነምግባሮች ሊያካትቱ ይችላሉ፣ እናም ስለዚህ በMCPS ደንብ JHC-RA፣ *የልጅ ማንሳቆልና ቸልተኝነት ዘገባ እና ምርመራ፣*

[1]እና/ወይም ከህግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ጋር በተገቡ የጋራ ስምምነቶች መሰረት ዘገባ ማድረግ ይጠይቃሉ። MCPS ማንኛቸውንም የውስጥ ምርመራዎችን ምርመራ ከሚያካሂዱ ከውጭ የህግ አስከባሪ ወኪል ድርጅቶች ጋር ሙሉ በሙሉ ተባባሪ በሆነ፣ እና የውጩን ምርመራ ጣልቃ በማይገባበት ወይም አደጋ በማያደርስበት መንገድ ማካሄድ አለበት።

A. በተማሪዎች ላይ ትግባሬ

1. የMontgomery County የትምህርት ቦርድ መምርያ፣ ACF፣ *ፆታዊ ወከባ*፣ በማናቸውም ፆታ ተማሪዎች በተማሪዎች ላይ ወይም በተቃራኒ ወይም በተመሳሳይ ፆታ ሰራተኛ ላይ የተፈፀመ የማይገባ ስነምግባር ነው።

2. ከፆታዊ ወከባ ወይም የፆታዊ ባህርይ ያለው ተገቢ ያልሆነ ስነምግባር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በሚመለከት ተማሪዎች አመራር፣ ድጋፍ፣ እና/ወይም ጥብቅና መጠየቅ/መፈለግ ይችላሉ። ከት/ቤት ሰራተኞ በተጨማሪ በካውንቲው የት/ቤት አስተዳደር ፅ/ቤት የሰራተኛ አባሎች ለነዚህ አገልግሎቶች ይገኛሉ።

3. ቅሬታ አመዘጋገብ

   a) ፆታዊ ወከባ ደርሶብናል ብለው የሚያምኑ የMCPS ተማሪዎች የዚህን አይነት ድርጊት ወድያውኑ ማስታወቅ አለባቸው።

      (1) ማስታወቂያ/ዘገባው በቃል ወይም በፅሁፍ ሊደረግ ይችላል።

      (2) ዘገባው ለማንኛውም የሰራተኛ አባል ሊደረግ ይችላል። የሰራተኛ አባል ተማሪው(ዋ)ን ለርእሰመምህር ወይም ተወካይ በMCPS ፎርም 230-35፣ *የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ ፎርም* በመጠቀም እንዲያስታውቀው/ቃት (እንዲያ(ድታ)ስታውቀው/ቃት) ያግዘዋል/ያግዛታል።

   b) አንድ ግለሰብ አንድን አድራጎት በማስታወቁ/ቋ፣ ወይም በተጠረጠረ አድራጎት ምርመራ በመሳተፉ/ፏ፣ በራሱ/ሷ ላይ ጎጂ እርምጃ አይወሰድም።

   አንድ ምርመራ በMCPS ደንብ JHF-RA፣ *ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት* መሰረት፣ በMCPS ፎርም 230-36፣ *የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት አድራጎት የት/ቤት ምርመራ ፎርም* በመጠቀም ይካሄዳል።

   d) ሚስጢራዊነት በሚመለከታቸው ህጎች እና በMCPS የመመርመርና እንደዚህ አይነት ቅሬታዎችን የመከታተል ባለበት ሃላፊነት መሰረት ይጠበቃል ።

   e) ግኝቶች እና ተገቢ እርምጃዎች በተቻለ ወቅታዊ መንገድ ይወሰዱ እና ለካውንቲው የት/ቤት አስተዳደር ፅ/ቤት ገቢ ይደረጋሉ።

   የቦርድ መመርያ ACF፣ *ፆታዊ ወከባን* የሚ(ምት)ጥስ ማንኛው(ዋ)ም ተማሪ፣ በMCPS ደንቦች JGA-RB፣ *የMCPS ተማሪ እገዳ ወይም ስንብት*፣ JGA-RC፣ *ስንክልና ያላቸው*

---

[1] ሙሉ ርእስ፡- *በMontgomery County Public Schools እና በMontgomery County የፖሊስ መምርያ እና በMontgomery County የሼሪፍ ፅ/ቤት እና የሮክቪል ከተማ የፖሊስ መምርያ እና በጌተስበርግ ከተማ የፖሊስ መምርያ እና በታኮማ ፓርክ ከተማ የፖሊስ መምርያ እና የMontgomery County ስቴት ኣቃቤ ህግ ፅ/ቤት መካከል የጋራ ስምምነት፡- የት/ቤት መገልገያ መኮንን ፕሮግራም እና ሌላ የህግ ኣስከባሪ ምላሾች በት/ቤት-ለተመሰረቱ ኣድራጎቶች (የጋራ ስምምነት)*

*ተማሪዎች እገዳ ወይም ስንብት፣ እና በየተማሪ ስነምግባር ኮድ በMCPS መሰረት* የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድብ(ባ)ታል። እንደ ጥቃቱ ከባድነት፣ የዚህ አይነቱ ተግባር፣ በነዚህ ሳይወሰን፣ ወደ ምክር፣ እገዳ፣ ወይም ስንብት ሊመራ ይችላል።

B. ትግባሬ በሰራተኞች

የቦርድ መመርያ ACF፣ *ፆታዊ ወከባ፣* እና ይህ ደንብ የMCPSን ሰራተኞች በሚያካትቱ በሁሉም የፆታ ወከባ አድራጎቶች ተግባራዊ ናቸው። መመርያውና ደንቡ ከሁለቱ በአንዱ ፆታ ያለው/ላት ግለሰብ በተቃራኒ ወይም ተመሳሳይ ፆታ ባለው/ባላት ግለሰብ የተፈፀሙ አድራጎቶችን ተመልክተው በMCPS ሰራተኞች የፆታ ወከባ ድርጊቶችን መፈፀም መመርያ መጣስ መሆኑን ያስቀምጣሉ።

2. የፆታዊ ወከባ ድርጊቶችን ማወቅና ወድያውኑ ተፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ የተቆጣጣሪ ሰራተኞች ሃላፊነት ነው።

3. ሰራተኞች ከፆታዊ ወከባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ወይም የጾታዊ ባህርይ ያለው ተገቢ ያልሆነ ስነምግባር ለመቋቋም ኣመራር፣ ድጋፍ፣ እና/ወይም ጥብቅና መጠየቅ ይችላሉ። Office of Employee Engagement and Labor Relations/የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሰራተኛ ግንኙነቶች ፅ/ቤት (OEELR) ለነዚህ ኣገልግሎቶች ይገኛል።

4. ቅሬታ ኣመዘጋገብ

a) ፆታዊ ወከባ ደርሶብናል ብለው የሚያምኑ የMCPS ሰራተኞች ኣድራጎቱን ወድያውኑ ማሳወቅ ኣለባቸው።

(1) ዘገባው በቃል ወይም በፅሁፍ ሊሆን ይችላል።

(2) ዘገባው ለOEELR ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ፣ ወይም ለተወካዮቻቸው ሊደረግ ይችላል።

b) ኣንድን ኣድራጎት በማስታወቅ፣ ወይም በተጠረጠረ ኣድራጎት ምርመራ ስለተሳተፈ/ች ወይም ስለተባበረ/ች፣ በግለሰብ ላይ ኣሉታዊ/ጎጂ እርምጃ ኣይወሰድም።

c) ሚስጢራዊነት በሚመለከታቸው ህጎች እና እነዚህን ቅሬታዎች በመሰሉ ቅሬታዎች ለመመርመርና ለመከታተል MCPS ባለው ሃላፊነት መሰረት ይጠበቃል።

d) ምርመራ በOEELR ይካሄዳል።

(1) የከውነቱ ኣጋጣሚ ሁኔታዎች በሙሉ በተጠረጠሩ ፆታዊ ወከባ ምርመራ ግንዛቤ ውስጥ ይገባሉ።

(2) የተጠረጠረው ስነምግባር ፆታዊ ወከባ ያካትት እንደሆነ ውሳኔ ኣውሳሰድን በሚመለከት፣ የኣድራጎቱ ዘገባ በኣጠቃላይ እና የሁኔታዎቹ ሙሉ በሙሉ፣ የተጠረጠሩት ኣድራጎቶች ኣውደ ናባብን ጨምሮ፣ ግንዛቤ ይደረግባቸዋል።

e) ግኝቶችና የውሳኔ ሃሳቦች በተቻለ መጠን በወቅቱ ይሰጣሉ።

f) የቦርድ *መመርያ* ACF፣ *ፆታዊ ወከባ* ወይም *ፆታዊ* ወከባን የሚመለከቱ የMCPS ደንቦችን ወይም ህጎችን የሚ(ምት)ጥስ ማንኛው(ዋ)ም ሰራተኛ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበ(ባ)ታል። የዚህ ኣይነቱ ተግባር በነሱ ሳይወሰን እነዚህን ያካትታል፡- ተግሳፅ፣ ሞያዊ ምክር፣ የስራ ዝውውር፣ ከስራ ደረጃ መውረድ፣ እገዳ፣ ወይም ስንብት።

C. ኣጠቃላይ መቀነባበር

የት/ቤት ኣስተዳደር ፅ/ቤት የዚህን ደንብ ተግባራዊነት ተማሪዎችን በሚመለከት ያስተባብራል፣ OEELR የዚህን ደንብ ተግባራዊነት ሰራተኞችን በሚመለከት እንደሚከተለው ያስተባብራል፡-

1. *ፆታዊ* ወከባን በሚመለከት ስለ ቅሬታ ኣፈታት፣ እና የኣመዘጋገብና ምርመራ ሂደቶች መረጃዎች ማሰራጨት

2. የተጠርጠሩ *ፆታዊ* ወከባን ለመፍታት የስልጠና ፕሮግራሞችን እና መመርያዎች መዳበርን መደገፍ

3. የተማሪ ቁሳቁሶች እድገት በት/ቤት ኣገልግሎት ላይ እንዲውሉ መደገፍ

4. ተማሪዎች የ*ፆታዊ* ወከባ ፕሮብሌሞችን እንዲገነዘቡና እንዲወጡ ለማገዝ እንቅስቃሴዎችንና ከሂሎት ግንባታን የሚያዋህዱ የK-12 የስርኣተትምህርት መሻሻሎች እድገትን መደገፍ

5. በMCPS ውስጥ የተማሪዎችና የሰራተኞች የሁለቱንም የ*ፆታዊ* ወከባ ቅሬታዎች ምርመራ፣ ሰነዳ፣ እና ማስታወቂያ ለት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ማመቻቸት

6. የ*ፆታዊ* ወከባ ቅሬታዎች ምላሽ ኣሰጣጥ ሂደቶች ትግባሬን መቆጣጠር

7. በቅሬታዎች ኣመዘጋገብ ስርኣት፣ ዘገባዎች እና በተከታይ የኣስተዳደር ተግባር ከሚስጢራዊነት መስፈርቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ መከበራቸውን መንከባከብ

8. ስለተዘገቡ የ*ፆታዊ* ወከባ ኣድራጎቶች የየሩብ ኣመት ዘገባ ማቅረብ። ዘገባዎቹ የሚያካትቱት

   a) ለሁለቱም የMCPS ሰራተኞችና ተማሪዎች የብዛትና የኣይነት ወራዊ የኣድራጎት ስብስብ ኣሃዝ/መረጃ፣

   b) የቅሬታና የመፍትሄ ሂደት ግምገማዎችና መሻሻሎች፣

   c) የስልጠና ስታቲስቲኮችና ፕሮግራሞች፣

   d) በሁሉም የMCPS ት/ቤቶች፣ ፅ/ቤቶች፣ እና የስራ ቦታዎች የስራ ኣካባቢዎች ቀጣይ ግምገማ፣ እና

   e) ለ*ፆታዊ* ወከባ መመርያ ስኬታማ ትግባሬ ኣስፈላጊ የሆኑ በMCPS ፕላን በመደረግና በመከናወን ላይ የሚገኙ ሌሎች እንቅስቃሴዎች።

D. የመረጃዎች ስርጭት

ፆታዊ ወከባን፣ ፆታዊ ወከባ ምን እንደሆነ፣ ግለሰቦች ምን ማድረግ እንደሚችሉ፣ እና ለእርዳታ የት እንደሚኬድ ስለሚመለከቱ የቦርድ መመርያዎች፣ እና ስለ የMCPS ደንቦችና ህጎች የMCPSን ሰራተኞችንና ተማሪዎችን የሚያስታውቋቸው ህትመቶች እና የመረጃዎች ስርጭቶች ይኖራሉ። ስለ ፆታዊ ወከባ መርጃዎች በOEELR እና በት/ቤት ኣስተዳደር ፅ/ቤት፣ ከስርኣተትምርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ፅ/ቤት ጋር በመገናኘት፣ ይዳብራሉ።

መረጃዎች፣ በነዚህ ሳይወሰኑ፣ በሚከተሉት በተለያዩ መንገዶች ይሰራጫሉ፡-

1. የስልጠና ዎርክሾፖች እና/ወይም መስመር ላይ ሞዱዩሎች፣

2. መግለጫ ፅሁፎች፣

3. መፅሄቶች፣

4. መተግበርያዎች፣

5. ማስታወቂያዎች፣ እና/ወይም

6. ሌሎች መገናኛዎች፣ እንደኣስፈላጊነቱ

E. ስልጠና

1. ለተቆጣጣሪ ሰራተኞች የሚሰጠው ስልጠና፣ በእነዚህ ሳይወሰን፣ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

   a) ፆታዊ ወከባን በሚመለከት የተግባራዊ ህጎችና መምርያዎች ድህረ እይታ፣

   b) ፆታዊ ወከባ የሚያካትቱ ኣድራጎቶችን ሲያያዙ/ሲጋፈጡ እንደ የስራ ቦታ ኣስተዳዳሪዎች ስራዎቻቸው፣ ሃላፊነቶች፣ እና እምቅ ተጠያቂነቶች፣

   c) ሰራተኞቻቸውን ለማሰልጠን መመርያዎች፣

   d) ለፆታዊ ወከባ ቅሬታዎች ምላሽ መስጫ መመርያዎች፣

   e) የሰራተኛ ቅሬታዎች መመርመርያ መመርያዎች፣

   f) የተማሪ ቅሬታዎች መመርመርያ መመርያዎች፣ እና

   g) ተከታታይ ድጋፍ መስጫ መመርያዎች።

2. የት/ቤት ርእሰመምህራን ተማሪዎች እንዲያውቁ፣ እንዲገነዘቡ፣ እና ፆታዊ ወከባ እንዲከላከሉ ለማገዝ የሚከተሉትን የሚያካትት ፕላን ለማዳበርና ለመተግበር ሃላፊነት ኣለባቸው፡-

   a) ለፆታዊ ወከባ ምላሽ መስጫ መመርያዎች፣

   b) በት/ቤት፣ ስራ፣ እና ማህበራዊ ኣከባቢዎች ተገቢ ላልሆኑ ፆታዊ ኣቅርቦቶችና ተፅእኖዎች

አንፃር የሚያለዝቡ/የሚያሻሽሉ ስነምግባሮችና አቋሞች ለማዳበር የተተለሙ እድሎች፣ እና

c) *ፆታዊ* ወከባን በሚመለከቱ የMCPS ተማሪ ቁሳቁሶች መጠቀም።

**የተዛመዱ ርእሶች:-** *የ1964 የሲቪል መብቶች ሕዋጅ፣* Title VII፤ *የ1972 የትምህርት ማሻሻያዎች ሕዋጅ፣* Title IX፣ እንደተሻሻለ፤ Equal Employment Opportunity Commission/የቅጥር እኩል እድል ኮሞሽን (EEOC) *የፆታዊ ወከባ መመርያዎች* (29 C.F.R. §1604.11)፤ የሜሪላንድ አኖቴትድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-424፤ *የጋራ ስምምነት*[2]፤ MCPS *የተማሪ ስነምግባር ኮድ*፤ MCPS *የተማሪ ስነምግባር ኮድ*

***የደንብ ታሪክ:-*** አዲስ ደንብ፣ ፌብሩወሪ 17፣ 1993፤ ፌብሩወሪ 22 2006 የተከለሰ፤ ጁላይ 31፣ 2017 የተከለሰ።

[2] ሙሉ ርእስ:- *በMontgomery County Public Schools እና በMontgomery County የፖሊስ መምርያ እና በMontgomery County የሼሪፍ ፅ/ቤት እና የሮክቪል ከተማ የፖሊስ መምርያ እና የጌተርስበርግ የፖሊስ መምርያ እና የታኮማ ፓርክ የፖሊስ መምርያ እና የMontgomery County ስቴት የኣቃቤ ህግ ፅ/ቤት:- የት/ቤት መገልገያ መኮንን ፕሮግራም እና ሌሎች የህግ ኣስከባሪ ምላሾች በት/ቤት ለተመሰረቱ ኣድራጎቶች (የጋራ ስምምነት)*